የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 32
ADDIS ABABA 8th June, 2012

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፪/፪ሺ፬ ዓ.ም

የተባበሩት መንግሥታት የባሕር ሕግ ኮንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ …... ገጽ ፮ሺ፫፻፵፪

Proclamation No.742/2012

United Nations Convention on the Law of the Sea Ratification Proclamation. ... Page 6342

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፪/፪ሺ፬

## PROCLAMATION No. 742/2012.

## የተባበሩት መንግሥታት የባሕር ሕግ ኮንቬንሽንን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE UNITED NATIONS CONVENTION ON THE LAW OF THE SEA

የተባበሩት መንግሥታት የባህር ህግ ኮንቬንሽን እ.አ.አ ዲሴምበር ፲ ቀን ፲፱፻፹፪ በጃማይካ ሞንቴጎ ቤይ ተፈርሞ እ.አ.አ ከኖቬምበር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፬ ጀምሮ በስራ ላይ የዋለ በመሆኑ፤

WHEREAS, the United Nations Convention on the Law of the Sea was adopted at Montego Bay, Jamaica, on 10 December 1982 and came into force on 16 November 1994;

ይህንኑ ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Convention at its session held on the 17th day of May, 2012;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተባበሩት መንግሥታት የባሕር ሕግ ኮንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፪/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "United Nations Convention on the Law of the Sea Ratification Proclamation No. 742/2012".

## ፪. <u>የኮንቬንሽኑ መጽደቅ</u>

እ.አ.አ በዲሴምበር ፲ ቀን ፲፱፻፹፪ በጃማይካ ሞንቴጎ ቤይ የተፈረመው የተባበሩት መንግሥታት የባሕር ሕግ ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. <u>የትራንስፖርት ሚኒስቴር ስልጣን</u>

የትራንስፖርት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ኮንቬንሽኑ በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. <u>Ratification of the Convention</u>

The United Nations Convention on the Law of the Sea adopted at Montego Bay, Jamaica, on 10 December 1982 is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Transport</u>

The Ministry of Transport is hereby empowered to undertake, in cooperation with the concerned governmental organs, all acts necessary for the implementation of the Convention.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of June, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**